# <u>በቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 1026/2017 ማሻሻያ ረቂቅ ላይ የቀረበ አጭር ማብራሪያ</u>

## 1. <u>የማሻሻያው አስፈላጊነት</u>

የአገራችንን የወጪ ንግድ ለማስፋፋት ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የግብይት ሥርዓት በተጨማሪ ቀልጣፋ እና ለህገወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ ያልተጋለጠ አማራጭ የግብይት ሥርዓት መዘርጋት ያለውን ከፍተኛ ጠቀሜታ ታሳቢ በማድረግ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 1026/2017 ወጥቶ ከመስከረም 2017 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ እንደዋለ ይታወቃል፡፡ የግብይት ሥርዓቱን ለማዘመን እና ተዓማኒነቱን ለማረጋገጥ በመመሪያው የተዘረጉትን የአሰራር ለውጦች የቅባት እህሎችን እና የጥራጥሬ ምርቶችን የግብይት ሥርዓት በማሳለጥ ረገድ የታለመላቸውን ዓላማ በተሻለ ሁኔታ እንዲያሳኩ በትግበራ ወቅት የታዩ ጠንካራ ጎኖችን ማስፋፋት እና እንደ ክፍተት የታዩ ጉድለቶችን ደግሞ ማሻሻል የሚጠበቅ ጉዳይ ነው፡፡

ከዚሁ አንጻር በአፈጻጸም ሂደት የግብይት መመሪያው የታለመለትን ዓላማ በተሻለ ሁኔታ እንዲያሳካ በመመሪያው ከተካተቱት አሰራሮች ውስጥ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች ላኪዎች (Exporters) በአማራጭ የቀጥታ ግብይት ሥርዓቱ ከምርት አቅራቢዎች ለገዙት ምርት በባንኮች በኩል ለአቅራቢዎች በቀጥታ የሚፈጽሙት የክፍያ ሥርዓት አማራጭ ግብይቱን ከማሳለጥ አንጻር የተወሰኑ ክፍተቶች የታዩበት መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ እንደማሳያም;

- በአቅራቢና በላኪ መካከል ከክፍያ አለመፈጸም ጋር የተያያዙ (Payment Default) ችግሮች እየተስተዋሉ መሆናቸው፣
- ከታክስ አሰባሰብ ጋር በተያያዘ በወቅቱና በትክክለኛው የግብይት ስርዐት የተፈጸሙ ግብይቶች ለመንግስት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ የሚፈጸምበት አግባብ ላይ ክፍተቶች መስተዋላቸው፣
- በአቅራቢና ላኪ መካከል የሚከናወኑ ግብይቶች የተጋነኑ ከመሆናቸው ባሻገር በትክክለኛው የክፍያ ስርዐት ባለማለፋቸው ምክንያት በላኪዎች ስም ተመዝግበው የሚገኙ የምርት መጠኖች ተአማኒነት ማጣታቸው፣



የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade and Regional Integration Archives
መዝገብ ቤት

CamScanner

- የወጪ ምርት አፈጻጸምን ለማሳደግ በሚኖረው የክትትልና ድጋፍ ስርዐት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑ የሚሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

እነዚህን ክፍተቶች ለመድፈን አማራጭ የግብይት ሥርዓቱ የበለጠ ግልጽ፣ ቀልጣፋ፣ ተዓማኒ እንዲሆን እና አቅራቢዎች የሸጡበትን ገንዘብ በወቅቱ ያለምንም መዛነፍ ሊያገኙ የሚችሉበትን አስተማማኝ የክፍያ ሥርዓት ባካተተ ሁኔታ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለፉት አስራ ሰባት አመታት በተግባር የተፈተነ፣ የሻጮችን የምርት ሽያጭ ገንዘብ ግብይቱ በተፈጸመ ማግስት በተቀላጠፈ እና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ የማስተላለፍ አሠራር ሲተገበር መቆየቱ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት ሥርዓት መመሪያ ከተሰጠው የሚዛን አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት በተጨማሪ በአማራጭ ግብይቱ ገገርዎች ለምርት አቅራቢዎች የሚፈጽሙት ክፍያ  በምርት ገበያው የክፍያ ሥርዓት በኩል እንዲፈጸም በሚያስችል መልኩ ማሻሻያ ቢደረግበት አማራጭ የግብይት ሥርዓቱ ቀልጣፋ፣ ተዓማኒ እንዲሆን እና የግብይት ሥርዓቱን የህግ ተገገርነት ከማረጋገጥ አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል ታምኖበታል፡፡

2. <u>የማሻሻያው ይዘት</u>

ረቂቅ መመሪያው በአጠቃላይ ሦስት አንቀጾችን ያካተተ ነው፡፡ በአንቀጽ አንድ የመመሪያው አጭር ርዕስ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 1026/2017ን እንደገና ለማሻሻል የወጣ መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን አንቀጽ 2 የተደረጉትን ማሻሻያዎች በዝርዝር የሚያስቀምጥ ነው፡፡ የመጨረሻው አንቀጽ ሦስት ደግሞ መመሪያው የሚጸናበትን ጊዜ ያመለክታል፡፡

የረቂቅ መመሪያው የማሻሻያ አንቀጽ 2 ሦስት ማሻሻያዎችን ያካተተ ሲሆን በአጠቃላይ ሲታይ በክፍያ አፈጻጸም  ዙሪያ የተደረገ ነው፡፡ በሥራ ላይ ባለው የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 1026/2017 (እንደተሻሻለው) የተዘረጋው የግብይት ሥርዓት አቅራቢዎች እና ላኪዎች ምርቱን በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከማስመዘን በስተቀር በቀጥታ በሚደረግ ግንኙነት እንዲገበያዩ፣ የምርቱን መጠን፣ ጥራት፣ ዋጋ፣ የርክክብ እና የክፍያ አፈጻጸም በራሳቸው እንዲወስኑ የሚያስችል መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከዚህ በላይ በመግቢያው የተጠቀሱትን ክፍተቶች ለመድፈን ሲባል ሌሎች የቀጥታ ግብይቱ የአሠራር ሥርዓቶች እንደተጠበቁ ሆነው በክፍያ አፈጻጸም ላይ ብቻ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡



የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade and Regional Integration Archives
መዝገብ ቤት

ማሻሻያ ከተደረገባቸው አንኳር ጉዳዮች መካከል በግብይት መመሪያው አንቀጽ 6 ስር የተካተተው የክፍያ አፈጻጸምን የሚመለከተው ድንጋጌ በዋናነት ይጠቀሳል፡፡ ላኪው ለተረከበው የቅባት እህል ወይም የጥራጥሬ ምርት ርክክብ በተፈጸመ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለአቅራቢው ሙሉ ክፍያ በባንክ በኩል በአንድ ጊዜ መፈጸም እና የባንክ የክፍያ ደረሰኝ መያዝ እንዳለበት ግዴታ የሚጥለው የመመሪያው አንቀጽ 6 ክፍያ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የክፍያ ሥርዓት በኩል በአስገዳጅነት የሚያልፍበትን ሁኔታ በሚያመለክት መልኩ ተሻሽሎ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ ሌሎች ማሻሻያዎች በአንቀጽ 8 (4) እና (5) እና አንቀጽ 15 (7) ላይ ከቀድሞው የክፍያ ሥርዓት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን አዲስ ከተዘረጋው የክፍያ ሥርዓት ጋር ለማጣጣም የተደረጉ ናቸው፡፡

ስለሆነም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የመመሪያውን አስፈላጊነት ተገንዝቦ ያጸደቀው ስለሆነ በአስተዳደር ሥነሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሠረት እንዲመዘገብልን በአክብሮት አቅርበናል፡፡

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade and Regional Integration Archives
መዝገብ ቤት



CS CamScanner

# መመሪያ ቁጥር 1115/2018

## የቅባት እህሎችን እና የጥራጥሬ ምርቶችን የቀጥታ ግብይት ለመወሰን የወጣውን መመሪያ እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

የቅባት እህሎችን እና የጥራጥሬ ምርቶችን የቀጥታ ግብይት ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 1026/2017 እንደገና ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19(4) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

**ይህ መመሪያ "የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 1026/2017ን እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 1115/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡**

2. **ማሻሻያ**

የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 1026/2017 (እንደተሻሻለው) እንደገና እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1) የመመሪያው አንቀጽ 6 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 6 ተተክቷል፡፡

"6. ስለ ክፍያ አፈጻጸም "

1/ ላኪው ለገዛው የቅባት እህል ወይም የጥራጥሬ ምርት የመግዣ ዋጋውን ለዚሁ አላማ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በተከፈተው የመግዣ ገንዘብ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

2/ አቅራቢ እና ላኪ ከተገበያዩ በኋላ ክፍያ እንዲፈጸም በጽሁፍ ሲጠይቁ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ቀጥሎ ባለው የሥራ ቀን የመግዣ ዋጋውን በአቅራቢው የባንክ ሂሳብ ማስተላለፍ አለበት፡፡"

2) የመመሪያው አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) ተተክተዋል

"4/ የመግዣ ዋጋን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለዚሁ ዓላማ በከፈተው የባንክ ሂሳብ ውስጥ የማስገባት እና የባንክ ስሊፕ የመያዝ፤

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade and Regional Integration Archives
መዝገብ ቤት

5/ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተሰጠውን የምርት ምዘና እና የተጣራ የግብይት ግዴታ ሪፖርት ሰነድ በማቅረብ ከሚኒስቴሩ የኮንትራት ምዝገባ እና የኤክስፖርት የመላኪያ ፈቃድ የማግኘት፤"

3) የመመሪያው አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (7) ተሰርዟል፡፡ ከንዑስ አንቀጽ (8) እስከ ንዑስ አንቀጽ (12) የነበሩት እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ (7) እስከ ንዑስ አንቀጽ
(11) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

3. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በሚኒስቴሩ ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ
ጥቅምት 20 ቀን 2018 ዓ.ም

ካሳሁን ጎፌ ባለሚ (ፒ.ኤች.ዲ)
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር



CamScanner